# “አኬልዳማን” ይመልከቱ፤ መለስን ለማስወገድ ይነሱ!!!

ህዳር 23 ቀን 2004 ዓም ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በበረከት ስምኦን እና ሺመልስ ከማል አዘጋጅነት የተሠራውና “አኬልዳማ” የተሰኘውን አዲስ ፊልም ኢትዮጵያዊያን እንዲያዩት ይመክራል። የፊልሙ አዘጋጆች ሰዓት ለማብዛት የጨመሯቸውን ክፍል አንድና ሁለት የታሪኩ አካል ስላልሆኑ ቢታለፉም ምንም ችግር የለውም። ክፍል ሶስትን በትዕግሥት ከተመለከቱ ግን ቢያንስ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛሉ ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

1. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ምን ያህል ፈሪ እና በፍርሃቱም ምክንያት ምን ያህል ጨካኝ እንደሆነ ይረዳሉ። አገዛዙ እጁ ውስጥ የገቡ ሰዎችን ለማዋረድ የቱን ያህል ርቀት እንደሚሄድ ይታዘባሉ። ይህ የሥርዓቱ ባህርይ ገላጭ በመሆኑ ሁለገብ የትግል ስትራቴጂ ለምን እንደተመረጠ ይገነዘባሉ፤ እርስዎም ይቆርጣሉ። ይህንን ግፍ በዜጎቹ ላይ የሚፈጽም ሥርዓት ውሎ ማደር የሌለበት መሆኑን ይረዳሉ።
2. “የመለስ ዜናዊ ሥርዓት መወገድ አለበት” የሚሉ እርስዎ ብቻ አለመሆንዎ ፊልሙ በተዘዋዋሪ መንገድ በመንገር ብርታት ይሰጥዎታል። አትኩረው ያዳምጡ!!! የግንቦት 7 አባላት በርካቶች መሆናቸው፤ በጥሩ ሁኔታ መደራጀታቸውና መቁረጣቸው ይነግርዎታል። በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ. ም. የነበረን ተስፋ መነጠቃችን ያንገበገባቸው የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ታጋዮች አጠገብዎና እጎንዎ እንዳሉ ፊልሙ ይነግርዎታል።
3. የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በግንቦት 7 የተግባር ሥራ ግራ መጋባቱ እና የሚይዘውና የሚጨብጠው የጠፋበት መሆኑን ይረዳሉ። ከጥቂት ጊዜዓት በፊት “ግንቦት 7 ወታደራዊ መዋቅሬን ቦርቡሮ መፍንቅለ-መንግሥት ሊያኪሂድብኝ ነበር” ብሎ ነበር። አሁን ደግሞ “ህጋዊ ተቃዋሚዎቼን ለዓላማው ማስፈፀሚያ አሰለፈብኝ” ይልዎታል። በዚሁ ፊልም “የግንቦት 7 አባላት እፍኝ አይሞሉም፤ አበነንኳቸው” ካለ በኋላ ወዲያው ደግሞ “ሴራቸው አላለቀም፤ የድርጅቴን መሪዎችና የአገዛዜን ባለሥልጣናት ሊገድሉብኝ ነው። ሕዝብ ሆይ! እንቅልፍ አጥተህ ዘብ ቁምልኝ” ሲል ያስደምሞታል። እንደ ጋዳፊም “ሕዝብ ይወደኛል፤ ይጠብቀኛልም” እያለ ያስቅዎታል።
4. እርሱ ራሱ በሻብያ ጀርባ ላይ ተንጠልጥሎ አራት ኪሎ እንዳልገባ ሁሉ “በሻብያ እየተረዱ ሊመጡብኝ ነው” ብሎ እሪ ብሎ ሲጮህ በመስማት ይዝናናሉ። እንዲሁም ሥልጣን ከመያዙ በፊት የሃገሪቱን ባንኮች፣ የጭነት መኪናዎችና አውቶቡሶች እየዘረፈ በሱዳንና በአረብ ሃገሮች የንግድ ሥራውን እንዳላጦፈ፤ ሥልጣን ከያዘም በኋላ ሌላው ሁሉ ቀርቶ የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው መረጃ መሠረት 8. 4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መስረቁን፤ ለም መሬታችን እየሸጠ መሆኑን፤ በብሄራዊ ባንክ ተቀምጦ የነበረውን ወርቅ በባሌስትራ ብረት ተክቶ መስረቁን ስለሚያውቁ “ግንቦት 7 ባንኮቼን ሊዘረፍ አስቧል” እያለ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል እያዩ ይስቃሉ።

5. ሰላማዊ ሰልፍ መጥራት፤ ከወዳጅዎ ጋር ኢሜል መፃፃፍ፤ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ከጠራ ፓርቲ መሪ ጋር መነጋገር ከፍተኛ ወንጀል እንደፈጸመ ሰዉ በእድሜ ልክ ወይም በሞት የሚያስቀጡ መሆናቸውን ሲረዱ "እንዴት አድርጌ ልታገል" ለሚለው ጥያቄዎ ምላሽ ያገኛሉ። ሙብት እንዲከበርልዎ መለመንም ሆነ መጠየቅ እኩል የሚያስቀጡ ከሆነ የትኛውን መምረጥ እንዳለብዎ "አኬልዳማ" ግልጽ በሆነ መንገድ ይነግርዎታል። ።
6. የመለስ አገዛዝ ካልተገደደ በስተቀር በፈቃዱ ከዘረኛና አምባገነናዊ አቋሙ ፈቀቅ እንደማይል በማያሻማ ሁኔታ ከፊልሙ ይገነዘባሉ።
7. በዘረኛው መለስ ዜናዊ የሥልጣን ዘመን ከቀድሞ አገዛዞች በላቀ ሁኔታ ሰቆቃና ግርፋት "ልማታዊ እድገት" ማሳየታቸው በቀላሉ ማየት ይችላሉ። በገራፊዎችና ሰቆቃ ፈፃሚዎች እጅ ውስጥ ያሉ ንፁሃን ዜጎች ገራፊዎችን የሚያስደስት ነገር ሊናገሩ እንደሚችሉ ከፊልሙ ይረዳሉ።
8. በፊልሙ ውስጥ የወገኖቻችንን ስቃይ ሲመለከቱ መምህር የኔሰው ገብሬን ማስታወስዎ አይቀርም። መምህር የኔሰው ገብሬ ህግና መንግሥት አለ ብሎ የሕዝብን ጥያቄ በአቤቱታ ለማሰማት የጣረ ወጣት ነበር። አቤቱታው ያተረፈለት እስር፣ እንግልት፣ ውርደት ሆነ። ኅዳር 1 ቀን 2004 ዓም መምህር የኔሰው ገብሬ

> *በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!!*

ብሎ ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ ራሱን አቃጠለ። ኅዳር 4 ቀን ሕይወቱ አለፈች። ይህ የሆነው እኛው አገር ዳዉሮ ዞን፣ ዋካ ከተማ ውስጥ ነው። ፊልሙን እያዩ ልብዎ ወደ እርሱ መሄዱ አይቀርም። እርስዎም

> *እውነትክን ነው ወንድሜ የኔሰው፤ ይህንን ግፍ እያዩ መኖር ኑሮ አይባልም!!!*

ማለትዎ አይቀርም።

ስለሆነም "አኬልዳማን" ይመልከቱ፤ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ ቆርጠው ይነሱ!!!

በፊልሙ መጨረሻ ላይ እንደተነገረው ሁሉ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ታጋዮች የመለስን ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ አስጨንቀዋል። ይህ ደግሞ በበለጠ ኃይል ይቀጥላል። መለስና ግብረ አበሮቹ ማምለጫ የላቸውም። እርስዎም የዚህ ትግል አካል ይሁኑ!!! ይነሱ!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!